Ethiopian Academy of Sciences
የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ

---

<u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

**“ዝክረ አሊ ማዝሩዊ ፡ የአፍሪካዊውን ምሁር ሕይወት ውዳሴ”**
**የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋራ ያዘጋጁት የመታሰቢያ ዝግጅት**
**የካቲት 20 ቀን 2007 ዓ.ም**
**እሸቱ ጮሌ አዳራሽ፣ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋራ በጥቅምት ወር 2007ዓ/ም በቢንገሐምተን ኒው ዮርክ ሕይወታቸው ያለፈውን ፕሮፌሰር አሊ ማዝሩዊ ሕይወትና ሥራ ለመዘከር ያለመ ዝግጅት አርብ የካቲት 20 ቀን 2007ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ውስጥ በሚገኘው እሸቱ ጮሌ አዳራሽ ይካሔዳል፡፡

በትውልድ ኬንያዊ የሆኑት አሊ ማዝሩዊ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በዩናይትድ ኪንግደም ተከታትለዋል፡፡ የዩጋንዳው ማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ፣ ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ እና ቢንግሐምተን ዩኒቨርሲቲ ሙሁራዊ አስተዋፅኦ ካበረከቱባቸው ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ይገኙበታል፡፡

አሊ ማዝሩዊ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪ፣ መምህር፣ ፀሐፊና ሃያሲ ሲሆኑ ዋነኛው ሙሁራዊ አበርክቷቸውና የሁል ጊዜ መታወሻቸው የአፍሪካን ጥናት ከቅኝ ገዢዎች ቅኝት እንዲላቀቅ ማድረጋቸው ሲሆን የአፍሪካ ታሪክ እና ተግዳሮቶች በተለየ መነፅር እንዲታይም አስችለዋል፡፡ በኢምፔሪያሊዝም፣ በፂዮናዊነት፣ በዘረኝነት እና በማንኛውም አይነት ጭቆና ላይ ያቀርቡ የነበሩት ሂስ አፍሪካውያንም ሆኑ ሌሎች ማንኛውንም አይነት ኢፍትሐዊነት እንዲታገሉ አበረታቷቸዋል፡፡

አሊ ማዝሩዊ በኢትዮጵያና በኢትየጵያ ታሪክ ላይ ልዩ ፍቅር የነበራቸው ሲሆን ይህም በፁሑፋቸው፣ በአስተሳሰቦቻቸው እና በምልከታዎቻቸው ኢትዮጵያ በአፍሪካና በአለም ላይ የተሸለ ገፅታ እና ጥልቅ እይታ እንዲኖራት አስችለዋል፡፡

በዝክረ አሊ ማዝሩዊ ላይ ንግግር ከሚያደጉ እንግዶች መካከል የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዘደንት ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ፣ በኢትዮጵያ የኬንያ ሪፐብሊክ አምባሳደር ካትሪን ሞዋንጊ፣ ከሊደን ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ ተቋም ፕሮፌሰር ሞሀመድ ሳሊህ እና የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያና አለም አቀፍ አማካሪ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ታደሰ ይገኙበታል፡፡

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ በሚያዚያ 2002 ዓ.ም ከተለያዩ ዘርፎች በተወጣጡ 49 ኢትዮጵያውያን ምሁራን የተቋቋመ ሲሆን ዋና ዓላማውም ሁሉም የሳይንስ ዘርፎች እንዲጎለብቱ ማድረግ ነው፡፡ የአካዳሚው ተልዕኮም በሀገራችን የሳይንስ እና የምርምር ባህል እንዲያድግና አገር በቀል እውቀትን ጨምሮ የሳይንስ እውቀት እንዲጎለብት ማገዝ ነው፡፡ አካዳሚው በመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 783/2004 የተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፡፡